የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No. 58
ADDIS ABABA 28th August, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩ ዓ.ም

የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ… ገጽ ፬ሺ፰፻፵፫

CONTENTS

Proclamation No. 654/2009

Flag Proclamation …..Page 4843

## አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ

ስለ ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ ፫ ንዑስ አንቀፅ /፩/ እና /፪/ የተደነገገ በመሆኑ፤

ይህንን ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትለው ቀደም ሲል የወጡትና በስራ ላይ ያሉት ህጐች ሰንደቅ ዓላማን በሚመለከት ያልሸፈንዋቸው እና ያልተመለከትዋቸው ጉዳዮች በመኖራቸው፣

ለሕገ መንግሥቱ ድንጋጌ አፈፃፀም ሰንደቅ አላማንና አርማን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚወስን እና ቀደም ሲል የነበሩትን የተለያዩ ህጐች በአንድ ላይ የሚያጠቃልል አንድ ራሱን የቻለ ሕግ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፬/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 654/2009

## THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA FLAG PROCLAMATION

**Where as,** Article 3 sub-article /1/ and /2/ of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has declared the Flag of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

**Where as**, following this constitutional declaration the promulgated laws that are being enforced have not regulated and dealt with all Flag related basic issues;

**Where as,** it has been found necessary for the proper implementation of this constitutional declaration to provide for detailed issues pertaining to Flag as well as comprising all the previous laws as a single legal document;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article -55/1/ of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### GENERAL

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the " Flag Proclamation No. 654/2009 ".

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

፩/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ የፌዴሬሽኑ አባል ክልል ማለት ነው፤

፪/ "የከተማ መስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ወይም የድሬደዋ ከተማ መስተዳደር ማለት ነው፤

፫/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፬/ "በስተቀኝ" ማለት አንድ ሰው ፊቱን ወደ ተመልካች አቅጣጫ በማድረግ ሰንደቅ ዓላማዎች በሚቆሙበት ወይም በሚሰቀሉበት ወይም ባሉበት መስመር መሀል ሲቆም የሚኖረው የቀኝ እጅ አቅጣጫ ማለት ነው።

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ፦

፩/ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዛት ወሰን ውስጥ የክልል መንግሥታትንና የከተማ መስተዳድሮችን ጨምሮ፤ እና

፪/ በውጭ ሀገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላዎች፣ የኢትዮጵያ ንግድ መርከቦችና ጀልባዎች እና አውሮፕላኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት
## ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን

## ፬. የሰንደቅ ዓላማ ቀን

ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን /ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን" እየተባለ የሚጠራ/ በየዓመቱ መስከረም ሁለተኛ ሳምንት ሰኞ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል።

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1) **" Regional State"** means a Regional State member of the federation established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2) **"Administrative City"** means the Administrative City of Addis Ababa or the Administrative City of Dire Dawa;

3) **"Person"** means a natural or juridical person;

4) **"On the Right"** means on the extreme right with reference to the direction of a person standing in the line of flags facing observers.

## 3. Scope of Application.

This Proclamation shall be applicable.

1/ within the territorial boundary of the Federal Democratic Republic of Ethiopia including Regional States and Administrative Cities; and

2/ to Ethiopian citizens in foreign countries, embassies and consulates of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, merchant ships, boats and air planes registered in Ethiopia.

## PART-TWO
## National Flag Day

## 4. The Flag Day

The National Flag Day /hereinafter referred as "the National Flag Day"/ shall be celebrated at the national level every year on the second Monday of the Ethiopian month of Meskerem

## ክፍል ሦስት
## ስለ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ ዓርማ

### ፭. የሰንደቅ ዓላማ ምንነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ (ከዚህ በኋላ "ሰንደቅ ዓላማው" እየተባለ የሚጠራ) የሪፐብሊኩ ሉዓላዊነትና የሕዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት መግለጫ ነው።

### ፮. የሰንደቅ ዓላማው ቀለማትና ቅርፅ

፩/ ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሃል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ የተቀረፀ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል። ዓርማው በሰንደቅ ዓላማው መሃከል ላይ የሚያርፈው የክቡ ዙሪያ የአረንጓዴውንና የቀዩን ቀለማት ቁመት አጋማሽ አካሎ ይሆናል።

፪/ ቀለማቱ ብሩህና መሠረታዊ ይሆናሉ።

፫/ ቀለማቱ አግድም የተዋቀሩና እኩል ስፋት የሚኖራቸው ይሆናሉ፤ የሰንደቅ ዓላማው ወርድ የቁመቱ እጥፍ ይሆናል።

፬/ የዓርማው ቅርፅ ክብ በሆነ ሰማያዊ መደብ ላይ፦

ሀ/ ከየአቅጣጫው መጥተው የሚገናኙ ቀጥታና እኩል የሆኑ ቢጫ መስመሮች ይኖረዋል፤

ለ/ ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረ ኮከብ ይኖረዋል፤

ሐ/ ቀጥታና እኩል በሆኑት መስመሮች መተላለፊያ ላይ የሚፈነጥቅ ቢጫ ጨረር ይኖረዋል።

### ፯. የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም

የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል፡-

፩/ አረንጓዴው የሥራ፣ የልምላሜና የእድገት ምልክት ነው፤

፪/ ቢጫው የተስፋ፣ የፍትሕና የእኩልነት ምልክት ነው፤

፫/ ቀዩ ለነፃነትና ለእኩልነት መስፈን የሚደረግ የመስዋዕትነትና የጀግንነት ምልክት ነው።

## PART–THREE
## The Flag and the National Emblem

### 5. Symbolism of the Flag

The Flag of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (hereinafter "the Flag") symbolizes the sovereignty of the Republic and the unity of its peoples founded upon their common will.

### 6. Colors and Shape of the Flag

1/ The Flag shall have the colors: green at the top, yellow at the middle and red at the bottom together with a National Emblem of circular blue background. The Emblem shall be set at the centre of the Flag in such a way that its circumference curves on the midpoint of the width of both the green and red colors.

2/ The colors shall be bright and basic.

3/ The colors shall be structured horizontally and be of the same size. The length of the Flag shall be twice its width.

4/ The Emblem shall be a blue circle with depictions;

a) straight and equal lines of yellow that come from all directions and join each other;

b) a star formed by the straight and equal lines;

c) yellow rays radiating from the points where the straight and equal lines cross each other.

### 7. Meaning of the Colors of the Flag

The colors of the Flag shall represent the following meanings:

1/ the green for labor, fertility and development;

2/ the yellow for hope, justice and equality; and

3/ the red for sacrifice and heroism towards the prevalence of freedom and equality.

## ፰. የዓርማው ትርጉም

፩/ ክብ የሆነው ሰማያዊ መደብ ሰላምን ያመለክታል።

፪/ ቀጥታና እኩል የሆኑት መስመሮች፤ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እንዲሁም የሀይማኖቶችን እኩልነት ያመለክታሉ።

፫/ ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረው ኮከብ፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በመፈቃቀድ የመሠረቱትን አንድነት ያመለክታል።

፬/ ቢጫ ጨረር፤ በመፈቃቀድ አንድነት ለመሠረቱት ብሔር፣ ብሔረሰቦች የፈነጠቀውን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል።

## ፱. የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ

የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ እንደሚከተለው ነው፡-

### ክፍል አራት
### የሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀልና አጠቃቀም ስነስርዓት

## ፲. የሰንደቅ ዓላማው መጠን

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፮ ንዑስ አንቀፅ /፫/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው የሚከተሉት መጠኖች ይኖሩታል።

## 8. Meaning of the Emblem

1/ The circular blue background of the Emblem signifies peace.

2/ The straight and equal lines signify the equality of Nations, Nationalities and Peoples as well as of Religions.

3/ The star formed by the straight and equal lines signify the unity founded by the Nations, Nationalities and Peoples of Ethiopia of their common will.

4/ The yellow rays signify the bright prospect in sight for the Nations, Nationalities and Peoples united of their common will.

## 9. Pictorial Representation of the Flag

The pictorial representation of the Flag is as follows:

### PART-FOUR
### Procedure of Display and use of the Flag

## 10. Standard Sizes of the Flag

Without prejudice to Article 6(3) of this Proclamation, the standard size of the Flag shall be as follows:

| ተራ ቁጥር | የሰንደቅ ዓላማው ቁመት እና ወርዱ መጠን በሣንቲም ሜትር |
|---|---|
| ፩ | ፪፻፲x ፬፻፳ |
| ፪ | ፩፻፶x ፫፻ |
| ፫ | ፩፻፴፭x ፪፻፸ |
| ፬ | ፩፻፭x፪፻፲ |
| ፭ | ፺x፩፻፹ |
| ፮ | ፳፩x ፵፪ |

## ፲፩. የሰንደቅ ዓላማው መጠን አጠቃቀም

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፮/፫/ የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ቦታዎችና ክንዋኔዎች የሰንደቅ ዓላማው መጠን በዚህ አዋጅ በአንቀፅ ፲ በተደነገጉት መጠንን በሚመለከቱት ተራ ቁጥሮች መሠረት ይሆናል።

፩/ በከፍተኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፩ ይሆናል።

፪/ በመካከለኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፪ ይሆናል።

፫/ በመስሪያ ቤቶች፤ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ድርጅቶች አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፫ ይሆናል።

፬/ በትልልቅ የመንግሥት ህንፃዎች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፫ ይሆናል።

፭/ በትልልቅ ህንፃዎች ምድር ቤት ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችና የንግድ ቤቶች የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፬ ይሆናል።

፮/ በከፍተኛ መርከቦች ላይና በሰልፍ ጊዜ በክብር ዘብ የሚያዘው የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፬ ይሆናል።

| Flag Size No | The width and Length of the Flag in centimeter |
|---|---|
| 1 | 210x420 |
| 2 | 150x300 |
| 3 | 135x270 |
| 4 | 105x210 |
| 5 | 90x180 |
| 6 | 21x 42 |

## 11. Sizes for Display

Without prejudice to Article 6/3/ of this Proclamation in the following places and occasions the Flag shall be displayed in accordance with the standard sizes provided under Article 10 of this Proclamation:

1/ at major squares, the size of the Flag shall be Size No.1;

2/ at medium squares, the size of the Flag shall be Size No. 2;

3/ at the squares of offices, higher education institutions and organizations, the size of the Flag shall be Size No.3;

4/ on major government buildings, the size of the Flag shall be Size No. 3;

5/ at organizations and business enterprises on the ground floor of major buildings, the size of the Flag shall be Size No.4;

6/ on major ships and when displayed by a guard of honor in procession, the size of the Flag shall be Size No.4;

፯/ ለውጭ ሀገር እንግዳ አቀባበልና ለበዓላት በየመንገዱ ለሚውለበለብ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፭ ይሆናል።

፰/ በመካከለኛ መርከቦች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፭ ይሆናል።

፱/ በፕሬዝዳንቱ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩና በአምባሳደሮች ፅህፈት ቤት ጠረጴዛ ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር ፮ ይሆናል።

፲/ ፕሬዘዳንቱ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና አም ባሳደሮች በሚጓዙበት መኪና ላይ የሚውለ በለበው ሰንደቅ ዓላማ የቁመቱና የወርዱ ቅንብር /ሬሾ/ ፫ ለ፬ ሆኖ ፴ በ፵ ሣንቲም ሜትር ነው።

## ፲፪. የሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀል

፩/ የሰንደቅ ዓላማውን መውለብለብ የሚያግድ ከአ ቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተ ቀር፤ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በሚኒስ ትሮች ምክር ቤት፣ ከላይ እስከታች ባሉ የክልል የስልጣን አካላት ፅህፈት ቤቶች፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ በሌሎች አስፈፃሚ አካላት ፅህ ፈት ቤቶች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በመከላከያ ድርጅቶች፣ በፖሊስና በጠ ረፍ ጥበቃ ተቋሞች፣ በሪፐብሊኩ ኤምባሲ ዎችና በአምባሳደሮች መኖሪያ ቤት ሕንፃዎች እንዲሁም የሪፐብሊኩ ንግድ መርከቦች እና ጀልባዎች በየቀኑ ሰንደቅ ዓላማ ይሰቅላሉ።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ያልተመለ ከቱ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በብሔ ራዊ በዓል ቀን ሰንደቅ ዓላማ ይሰቅላሉ።

፫/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /፪/ የተደነገ ገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማ የሚሰ ቀለው በሚከተሉት ስፍራዎች ይሆናል፡-

ሀ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ፤

ለ/ በፌዴሬሽን ምክር ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ፤

ሐ/ የሪፐብሊኩ ፕሬዘዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር በፅህፈት ቤቱና በመኖሪያ ቤቱ ሕንፃዎች።

7/ in honor of foreign guests and on public holidays the size of the Flag flown in the streets shall be Size No.5;

8/ on medium size ships, the size of the Flag shall be size No. 5;

9/ on the desks of the offices of the President, the Prime Minister and Ambassadors, the size of the Flag shall be Size No.6;

10/ on vehicles in which the President, the Prime Minister and Ambassadors travel, the width and length shall be in the ratio of 3:4 and shall be 30 by 40 cent meter.

## 12. Display of the Flag

1/ Except in case of force majeure obstructive to having it flown the Flag shall fly daily at the House of Peoples' Representatives, at the Council of Ministers, at Regional organs of power at every level, at Ministries, at other executive organs, at courts, at schools, at military establishments, at police and border-guard establishments and at the embassies and residential buildings of Ambassadors of the Republic and merchant ships and boats of the Republic.

2/ Government offices not specified in sub article (1) of this Article shall fly the Flag on public holidays.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article /2/ of this Article the Flag shall fly at the following places:

a) at the square with in the premises of the House of Peoples' Representatives;

b) at the square within the premises of the House of Federation;

c) at the respective offices and residential buildings of the President and of the Prime Minister of the Republic.

፬/ የዚህ አንቀጽ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት ለሚካሄድ ምርጫ ሰንደቅ ዓላማው መራጮች በሚመዘገቡበት እና ድምጻቸውን በሚሰጡበት ቦታ ይሰቀላል።

፭/ ሰንደቅ አላማው ከማናቸውም ኮሌጆች፣ የስፖርት ቡድኖች እና ተቋማትን ጨምሮ ከሌሎች አርማዎች ጋር በሚሰቀልበት ጊዜ ከመሀልና በቁመቱ ልክ ከፍ ብሎ ይውላል።

## ፲፫. የሰንደቅ ልሣን

የማንኛውም ሰንደቅ ልሣን /ጫፍ/ ግማሽ የክብ አምሳል ይኖረዋል።

## ፲፬. የሰንደቅ መትከያ ስፍራ

በአደባባይ የሚውለበለብ ሰንደቅ ዓላማ የሚተከለው በተቻለ መጠን ከሚተከልበት ተቋም ሕንፃ ፊት ለፊትና መሀል ለመሀል ይሆናል።

## ፲፭. ሰንደቅ ዓላማው የሚሰቀልበትና የሚወርድበት ጊዜ

፩/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፪/ እና /፫/ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፪/፩/ በተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም በመርከቦችና ጀልባዎች ላይ ሰንደቅ ዓላማው ከጠዋቱ በ፲፪ ሰዓት ተሰቅሎ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ይወርዳል። ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በታወጀባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የመከላከያ ሰራዊት አሀዶች ሁኔታው እስካልተለወጠ ድረስ መደበኛውን ሰዓት ጠብቀው ሰንደቅ ዓላማውን መስቀልና ማውረድ አይገደዱም።

፪/ በትምህርት ቤቶች ሰንደቅ ዓላማው የሚሰቀለው ጠዋት ተማሪዎች ተሰልፈው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ይሆናል፣ የሚወርደውም ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ይሆናል።

፫/ በበዓላት ወቅት ሰንደቅ ዓላማው ከዋዜማው እስከ በዓሉ ማግስት የሚሰቀል ሲሆን በነዚህ ቀናትም ጠዋት ፲፪ ሰዓት እየወጣ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ይወርዳል።

## ፲፮. ሰንደቅ ዓላማው አንድ ዓይነት ብቻ ስለመሆኑ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ ከዚህ በላይ በተደነገጉት አንቀፆች መሠረት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይና ክብ ሰማያዊ ቀለማት ኖሮት በመሀከሉ በዚህ አዋጅ የተዘረዘረው ዓርማ ያለው ብቻ ነው።

4/ Without prejudice to the generality of this Article the Flag shall be flown at the place where registration or casting takes place during election for the House of Peoples' Representatives.

5/ When the Flag is displayed with any other emblem including the emblems of college, sport clubs and institutions, it shall be at the center as higher as its proportional height.

## 13. Tip of the Flagstaff

The tip of any Flag staff shall be semi-circular in shape.

## 14. Place for Setting up the Flag Staff

The Flagstaff of the Flag flown at a square shall, as far as possible, be set up at the centre in front of the institution buildings.

## 15. Time of Hoisting and Lowering the Flag

1/ Without prejudice to sub-articles (2) and (3) of this Article, the Flag shall be hoisted at 6 a.m. and lowered at 6 p.m. at offices specified in Article 12(1) of this Proclamation as well as on ships and boats. However, military units in regions where a state of emergency has been declared need not comply with the regular hoisting and lowering times until the situation changes.

2/ In schools, the Flag shall be hoisted in the morning before closes begin and lowered at 6 p.m.

3/ The Flag shall be hoisted on the eve and lowered on the morrow of public holidays, however on each of these days the Flag shall be hoisted at 6 a.m. and lowered at 6 p.m.

## 16. Unity of the Flag

The Flag of the Federal Democratic Republic of Ethiopia shall only be of the colors of Green, Yellow, Red and blue circular background as provided hereinabove, together with the Emblem at centre, as specified in this Proclamation.

## ፲፯. ሰንደቅ ዓላማው ሲሰቀልና ሲወርድ ሊሠጠው ስለሚገባ አክብሮት

፩/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይህንን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠትና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት።

፪/ ብሔራዊ የሆነ ታሪካዊ ክስተት ወይም ሁኔታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰንደቅ ዓላማዎች ታሪክነታቸውን ለመጠበቅ በተዘጋጀ ቤተመዘክር እንዲቀመጡ ይደረጋል።

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው በሚያረጅበት፣ በሚቀደድበት ወይም በማንኛውም መልኩ ሊያገለግል ያልቻለ ሲሆን ተገቢው ክብርና ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ተሰጥቶት በማቃጠል እንዲወገድ ይደረጋል።

## ፲፰. ሰንደቅ ዓላማው ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል የሚኖረው የአወጣጥ ሥነ-ሥርዓት

፩/ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከክልል ሰንደቅ ዓላማ ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ ይውላል።

፪/ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሁለት ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከመሀል ሆኖ በቁመቱ ልክ ከሁለቱ ሰንደቅ ዓላማዎች ከፍ ብሎ ሲውል የክልሎቹ ሰንደቅ ዓላማዎች ደግሞ በክልሎቹ ስያሜና በአማርኛ ፊደል ተራ መሰረት ቀዳሚው በቀኝ ሌላው በግራ ይውላል።

፫/ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሁለት የበለጡ የክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ መጨረሻ ሲውል እሱን ተከትለው የክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች በክልሎቹ ስያሜና በአማርኛ ፊደል ተራ መሰረት ቦታቸውን ይይዛሉ።

## ፲፱. ሰንደቅ ዓላማው ከሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል የሚኖረው የአወጣጥ ስነስርዓት

፩/ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሌላ ሃገር ሰንደቅ ዓላማ ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል በስተቀኝ ይውላል።

## 17. Respect Due on Hoisting and Lowering of the Flag

1/ Any Ethiopian national shall have the responsibility and duty to pay due honor to the Flag of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

2/ The Flags related with a national historical phenomenon or event shall be kept at museums prepared for such purposes.

3/ When the Flag becomes old or worn out or in any way can no longer be used, it shall be destroyed by burning with the due respect.

## 18. Procedural Orders of Display of the Flag with the Flags of the Regional States

1/ When the Flag is displayed with a flag of a Regional State, it shall be placed on the right.

2/ When the Flag is displayed with two flags of Regional States, it shall be placed at the centre as higher as its proportional height and the other two flags shall be placed on the right and left of the Flag respectively according to the Amharic alphabetical orders of the names of the Regional States.

3/ When the Flag is displayed with more than two flags of Regional States, it shall be placed at the right end and, the flags of the Regional States shall be placed following the Flag according to the Amharic alphabetical order of the names of the Regional States concerned.

## 19. Procedural Order of Display of the Flag with the Flags of Foreign Countries.

1/ When the Flag is displayed with a flag of a foreign country it shall be placed on the right.

፪/ ከሁለት የሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከመሀል ሆኖ ሌሎቹ ሰንደቅ ዓላማዎች በሃገራቱ ስምና በእንግሊዝኛ ፊደል ተራ መሠረት ቀዳሚው በቀኝ ሌላው በግራ ይውላል።

፫/ ከሁለት ከበለጡ የሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በላቲን ፊደል ቅደም ተከተል ተራውን ይይዛል። ሆኖም ኢትዮጵያ አስተናጋጅ እንጂ የጉዳይ ተካፋይ ካልሆነች የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ መጨረሻ ይውላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ ፩ እስከ ፫ የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው በተባበሩት መንግስታት፣ በአፍሪካ ሕብረት እና በሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች ሰንደቅ አላማዎች ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ፳. በሰልፍ ጊዜ የሰንደቅ ዓላማው አያያዝ

ሰንደቅ ዓላማው በሕዝባዊ ሰልፍ እንዲያዝ ሲደረግ የአያያዙ ስነስርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፦

፩/ ሰንደቅ ዓላማውን የያዘው ሰው ከሰልፈኛው ፊት መሀል ለመሀል አምስት ሜትር ቀድሞ ይሄዳል፣

፪/ ተሸካሚው ሰንደቁን ከታች በቀኝ እጅ ከላይ በግራ እጁ በሰውነቱ መሀል ለመሀል ቀጥ አድርጎ ይይዛል፣

፫/ ሰንደቅ ዓላማው ይታጀባል።

## ፳፩. በተሽከርካሪዎች ላይ ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀም ሥነ-ሥርዓት

፩/ ማንኛውም የውጭ ሀገር ባለስልጣን ወይም የአለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት የስራ ኃላፊ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚመጣበት ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት በሚመድብለት ተሽከርካሪ የሚጓዝ ከሆነ፤ በማንኛውም ጊዜ በተሽከርካሪው በስተቀኝ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ የሚቀመጥ ሲሆን በስተግራ በኩል ደግሞ ባለሥልጣኑ ወይም ኃላፊው የተወከለበት ሀገር ወይም ተቋም ሰንደቅ ዓላማ ይቀመጣል።

2/ When the Flag is displayed with two flags of foreign countries, it shall be placed at the centre and the two flags shall be placed at the right and left of the Flag respectively on the basis of the English alphabetical order of the names of the countries.

3/ When the Flag is displayed with more than two flags of foreign countries, the Flag shall be placed following the English alphabetical order of the names of the countries, provided, however that Ethiopia is the host country but not participatory of the affair, the Flag shall be placed at right end.

4/ The provisions from sub-article- (1) to (3) of this Article shall be applicable mutandis mutatis with respect to the flags of the United Nations Organization, the African Union and any other international organization.

## 20. <u>Procedure at Procession</u>

At public procession the procedure of displaying the Flag shall be as follow:

1) the guard of honor in charge of holding the Flag shall come at front with five meter distance from the first group raw,

2) the guard of honor shall hold the staff with his right hand at its bottom and his left at the upper part by erecting at the center of his body,

3) the Flag shall be accompanied.

## 21. <u>Procedure to Mount and Fly the Flag on Vehicles</u>

1/ When a foreign official or an agent of international or continental organization travels in a car provided by the Ethiopian government, the Flag shall be flown on the right side of the car and the flag of the foreign country or the flag of the organization shall be flown on the left side .

፪/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም አምባሳደሮች የሚጓዙበት ተሽከርካሪ፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ መርከብ ወይም ጀልባ ላይ ሰንደቅ ዓላማው ይሰቀላል።

፫/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /፪/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሪፐብሊኩን ሰንደቅ ዓላማ በተሽከርካሪ ላይ በመስቀል መጠቀም የሚችሉት የሚከተሉት ብቻ ይሆናሉ፦

ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፤

ለ/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፤

ሐ/ የፌዴራል መንግስቱ ሚኒስትሮች፤

መ/ የሀገሪቱ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹም፤

ሠ/ የፌዴራል ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፤

ረ/ የክልል መንግስታት ፕሬዝዳንቶች።

## ፳፪. <u>በብሔራዊ ሀዘን ጊዜ ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት</u>

፩/ በኃላፊነት ላይ ያለ ወይም ከኃላፊነት የተነሣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በሚታወጀው ብሔራዊ የሐዘን ቀን ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ይደረጋል።

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ከተመለከቱት ሰዎች ውጪ ብሔራዊ የሀዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸው ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በውሳኔ የሚያልፍ ይሆናል።

፫/ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የብሔራዊ ሀዘን ቀኑ በህዝባዊና ሀይማኖታዊ በዓላት በሚውልበት ጊዜ ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ አይውለበለብም።

፬/ በዚህ አንቀፅ ድንጋጌ መሠረት በሚፈፀም የቀብር ሥነ-ሥርዓት ቀብሩ ከመፈፀሙ በፊት በአስክሬኑ ሣጥን ላይ ያረፈው ሰንደቅ ዓላማ በተገቢው ሥነ-ሥርዓት ተጣጥፎ መነሳት ያለበት ሲሆን በማንኛውም መልኩ መሬት እንዲነካ መደረግ የለበትም።

2/ The Flag shall be flown on the vehicle, train, air plane, vessel or ship in which the President, the Prime Minister or the Ambassador of the Federal Democratic of Ethiopia is traveling.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, the privilege of flying the Flag on a vehicle is restricted to:

a) the Speaker and Deputy Speaker of the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

b) The Speaker and Deputy Speaker of the House of Federation;

c) The Ministers of the Federal Government;

d) The Commander –in- Chief of the Army;

e) The Presidents of the Federal Courts;

f) The Presidents of the Regional States.

## 22. <u>Half-Masting and National Mourning</u>

1) In the event of the death of the President or the Prime Minister or the Deputy Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia on official duty or retirement , the Flag shall be flown at half-mast on the declared day of national mourning.

2) Up on the death of persons and dignitaries other than those mentioned under sub article-/1/ of this Article, half-masting and a national mourning day may be held if the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia pass a decision to that effect.

3) In cases where a national mourning day coincides with official holiday the Flag shall not be flown at half-mast.

4) On occasions of funeral in accordance with the provisions of this Article, the Flag shall first be folded following the appropriate procedure before the bier or coffin is lowered in to the grave. The Flag may not touch the ground.

## ክፍል አምስት
## የተከለከሉና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት

### ፳፫. የተከለከሉ ተግባራት

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

፩/ ሰንደቅ ዓላማውን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ዓርማውን ሳያካትቱ መጠቀም፤

፪/ ሰንደቅ ዓላማው ላይ ቃላቶችን መፃፍ፣ ሌሎች ምልክቶች ወይም አርማዎችን ወይም ስእሎችን ለጥፎ መገልገል፤

፫/ ያረጁ፣ የተበላሹ፣ ቀለማቸው የደበዘዘና የተቀደዱ ሰንደቅ ዓላማዎችን መጠቀም ወይም መገልገል፤

፬/ ሰንደቅ ዓላማው በወጣበት ሰንደቅ /ምሰሶ/ ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ ያለአግባብ ሌሎች ሰንደቅ ዓላማዎችን ወይም አርማዎችን ጨምሮ ማውለብለብ ወይም መገልገል፤

፭/ ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ሰንደቅ ዓላማውን በፅሁፍ ወይም በቃላት፣ ወይም በድርጊት ወይም በሌላ በማናቸውም አኳኋን መድፈር ወይም ማዋረድ ወይም ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ፤

፮/ የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት ቅደም ተከተል እንዲሁም የብሄራዊ አርማውን መጠን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገል፤

፯/ ሰንደቅ ዓላማውን በዚህ አዋጅ ከተጠቀሰው የማውረጃ ጊዜ በላይ ማቆየት፤

፰/ በስብሰባ ወይም በማናቸውም መሰል ክንውኖች ሰንደቅ ዓላማውን የጠረጴዛ ሽፋን አድርጎ መጠቀም፤

፱/ ሰንደቅ ዓላማን የህንፃ ወይም የሌሎች ቁሳቁሶች መሸፈኛ ማድረግ፤

፲/ ሰንደቅ ዓላማውን በማንኛውም ንግድ ማስታወቂያነት መጠቀም፤

፲፩/ ሰንደቅ ዓላማው በሚሰቀልበትና በሚወርድበት ጊዜ ተገቢውን ክብር አለመስጠት።

## PART FIVE
## Prohibitions and Penalties

### 23 Prohibited Activities

It is prohibited to commit any of the following:

1) to use the Flag without its Emblem as provided under this Proclamation;

2) to deface the Flag by writing or displaying sings, symbols, emblems or picture;

3) to use an old, faded or torn Flag;

4) to fasten advertisements, notices or other Flags or emblems on the staff of the Flag;

5) to disrespect, dishonor or damage the Flag by writing or word or act in public places;

6) to prepare or use the Flag without the proper order of its colors and size or its Emblem;

7) to fly the Flag beyond the permitted time;

8) to use the Flag for table or any other material covering at meetings or similar gatherings;

9) to use the Flag as a covering for a building;

10) to use the Flag in any form of commercial advertisement;

11) not to show the proper respect at the hoisting and lowering of the Flag;

## ፳፬. ቅ ጣ ት

፩/ በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፫ ከንዑስ አንቀፅ /፪/ እስከ /፲፩/ የተመለከቱትን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ እስከ ሶስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፫ ንዑስ አንቀፅ /፩/ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ እስከ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም አንድ አመት ከስድስት ወር በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

፫/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /፪/ የተመለከተውን ጥፋት የፈፀመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል እንደሆነ የገንዘብ ቅጣቱ ከሁለት እጥፍ ያላነስ ይሆናል።

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፭. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ ደንብ ለማውጣት ይችላል።

## ፳፮. መመሪያ ስለማውጣት

በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፳፭ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ተከትለው የሚከተሉት መስሪያ ቤቶች የአፈፃፀም መመሪያዎች ለማውጣት ይችላሉ፡-

፩/ የመከላከያ ሠራዊት አሀዶችን በሚመለከት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር፤

፪/ የንግድ መርከቦችንና ጀልባዎችን በሚመለከት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፤

፫/ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲዎችንና ቆንስላዎችን በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር።

## 24. Penalties

1) Without prejudice to the appropriate provisions of any other law, whosoever commits an act in contravention to the provisions of sub article /2/ to /11/ of Article 23 of this Proclamation shall be punishable with a fine up to 3000 birr or with rigorous imprisonment up to one year.

2) With out prejudice to any other appropriate provisions of a law, whosoever commits an act in contravention with sub-article /1/ of Article 23 of this Proclamation shall be punishable with a fine up to 5000 birr or rigorous imprisonment up to one year and six months.

3) Where the acts provided under sub-article/2/ of this Article are committed by a legal person, the punishment shall not be less than two times of the fine.

## PART–SIX
## Miscellaneous Provisions

## 25. Power to Issue Regulations

The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

## 26. Power to Issue Directives

The following organs of government may issue directives of implementation pursuant to regulations made in accordance with Article 25 of this Proclamation:

1) the Ministry of National Defince with respect to military units;
2) the Ministry of Transport and Communications with respect to merchant ships and boats;
3) the Ministary of Foreign Affairs with respect to the embassies and consulates of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## ፳፯. <u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፹፰ እና የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር ፵፰/፲፱፻፹፱ በዚህ አዋጅ ተተክተዋል።

## ፳፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 27. <u>Inapplicable Laws</u>

The Flag and Emblem Proclamation No. 16/1996 and the Flag and Emblem /as amended/ Proclamation No. 48/1996 are replaced by this Proclamation.

## 28. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of August, 2009**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**